# የጤና ባለሙያዎች ሙያዊ ሥነ-ምግባር፡ በአዲስ አበባ የጤና ተቋማት የሚታዩ የሥነ-ምግባር ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች፡-**

ስንዱ ተካልኝ

ፀደይ ግርማ

1 ትምህርትና ስልጠና፡- የህክምና ሥነ-ምግባር ትምህርት አስፈላጊ ስለሆነ በሃገሪቱ የጤና ትምህርት በካሪኩለም ተካቶ በወጥነት እንዲሰጥ የካሪኩለም ክለሳ ቢደረግ የተሻለ የጤና አገልግሎት ለመስጠት ያግዛል፡፡

2 ከዚህ በተጨማሪ ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ውጤታማነትን መመርመርና ተገቢውን የማሻሻል እርምጃ በመውሰድ ከሁሉም ቀዳሚ የሆነውን የባለሙያዎችን ብቃት ማነስ ችግር መከላከል አሊያም መቀነስ ያስፈልጋል፡፡ ባለሙያዎች የተፈጠረ ስህተትን በተመለከተ ስህተቱን ለሰራው ባለሙያ እንዲያስተካክል እንጂ ሪፖርት የማድረግ ሙያዊ ኃላፊነታቸውን አለመወጣታቸው ሪፖርት ቢያደርጉ ሊወሰዱ የሚችሉ ችግሩ ዳግም እንዳይከሰቱ ለማድረግ የሚስችሉ እርምጃዎች እንዳይወሰዱ በማድረግ ስህተቱ እንዲባባስ በር ይከፍታል፡፡ ስለሆነም ባለሙያዎች ሪፖርት የማድረግ ሙያዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡና ለተገልጋዮች ደህንነት ቅድሚያ እንዲሰጡ የትምህርትና ስልጠና ድጋፍ ማድረግ የመከላከል እርምጃ በመውሰድ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

3 የመረጃ አያያዝን ማሻሻል፡- ከጤና ባለሙያዎች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ በቂ መረጃ መኖር በዘርፉ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት መፍትሔ ለማምጣት ወሳኝ ቢሆንም በሃገር አቀፍ ደረጃ የጤና ባለሙያዎችን ሥነ-ምግባር፣ ሙያዊ ያልሆኑ ተግባራት ወይም የህክምና ስህተት አስመልክቶ የተቀናጀ መረጃ የለም፡፡ በፍርድ ቤቶች በባለሙያዎቹ ላይ የሚቀርቡ መዝገቦች ተለይተው የሚታወቁበት የመዝገብ አያያዝ የለም፡፡ ስለሆነም የጤና ባለሙያዎች ላይ በፍርድ ቤት የሚቀርቡ መዝገቦች ተለይተው እንዲታወቁ የመረጃ አያያዝ ቢሻሻል በባለሙያዎቹ ላይ የሚቀርቡ የክስ አይነቶችን፣ ብዛት፣ በየትኛው የሙያ ዘርፍ ያሉት እና ፍርድ ቤቶች እልባት የሰጡባቸውን አካሄድ በመዳሰስ የማሻሻያ ተግባራት

እንዲወሰዱ ማድረግ ይቻላል፡፡ የጤና ተቋማት እንዲሁም የፌደራልና የአዲስ አበባ የምግብ፣ መድኃኒትና ጤና እንክብካቤ ባለስልጣን መስሪያ ቤቶችም የተደራጀ የመረጃ አያያዝ በመተግበር ለጥናት አመቺ የሆኑ ሁኔታዎችን መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

4 የጤና ባለሙያዎችን ቁጥርና ጥራት መጨመር፡- መንግስት የጤና ሽፋንን ለማዳረስ የጤና ባለሙያዎችን ቁጥር በማሳደግ ረገድ እየሰራ ያለው ሥራ የሚበረታታ ቢሆንም የባለሙያዎችና የተገልጋዮች ቁጥር ተመጣጣኝ አለመሆኑ ባለሙያዎቹ ላይ ጫና በማሳደር ሙያቸውን በተገቢው ሁኔታ እንዳይወጡ ስለሚያደር ቁጥርን ማሳደጉ ላይ መሰራት አለበት፡፡ ያሉትም አንዳንድ ባለሙያዎች ቢሆኑም በቂ እውቀት ባለመቅሰማቸው የሕክምና ስህተት እየፈጠሩ በመሆኑ በአጠቃላይ በግልም ሆኑ በመንግስት የትምህርት ተቋማት በጤና የሙያ ዘርፍ የሚሰጥ የትምህርት አሰጣጡ ቢፈተሽና የማስተካከያ እርምጃዎች ቢወሰዱ የባለሙያዎችን ጥራት ለማሻሻል ይረዳል፡፡

5 የባለሙያዎች ፍልሰትን መቀነስ፡- የባለሙያዎች ፍልሰት ሃገሪቱ የጤና ባለሙያዎችን ለማብዛት የምታደርገው ጥረት ተግዳሮት ሆኗል፡፡ በመሆኑም የባለሙያዎቹ ቁጥር ከተገልጋዮቹ ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን የሰው ኃይሉን ከመጨመር ጎንለጎን የተማሩ የጤና ባለሙያዎችን ፍልሰት መቀነሱ ወሳኝ ነው፡፡ የጤና ባለሙያዎች ፍልሰትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ዘዴዎችን ለመቀየስ መንስዔውን በማጥናት የመከላከል እርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ ነው፡፡

6 የተገልጋዮችን ግንዛቤ ማሳደግ፡- የጤና ሥርዓቱ ላይ የተገልጋዮችን ተሳትፎ ለማሳደግ መረጃ የሚሰጡበት ነጻ የስልክ መስመር አገልግሎት መስጠቱ የሚበረታታ ቢሆንም ተሳትፎ ያለበቂ ግንዛቤ ሊተገበር የማይችል በመሆኑ የተገልጋዮች በመሠረታዊ የጤና አገልግሎቶች፣ አቅርቦቶች እና መብትና ግዴታቸውን እንዲያውቁ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ በሰፊው ሊተገበር ይገባል፡፡ ያለበቂ ግንዛቤ የማህበረሰቡ ተሳትፎ ሊታሰብ አይችልም፤ ያለማህበረሰብ ተሳትፎ የተሟላ የጤና ቁጥጥርን ለማድረግ

አዳጋች ያደርገዋል፡፡

7 የመሳሪያ ጥራትን መቆጣጠር፡- የጤና ተቋማት ስራ ከመጀመራቸውም በፊት ሆነ በስራ ላይ እያሉ ያልተቋረጠ ተገቢውን ቁጥጥር በማከናወን ችግር ባለባቸው የህክምና አጋዥ መሳሪያዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ በመሣሪያ ጥራት ጉድለት የሚከሰቱ ችግሮችን ለመቀነስ ይረዳል፡፡

8 በባለሙያዎች ላይ ተገቢውን ቁጥጥር ማድረግ እና እርምጃ መውሰድ፡- ሙያዊ ያልሆኑ ተግባራትን ለመከላከል ተገቢውን ቁጥጥር ማድረግ እና ጥፋተኛ የሆኑ ባለሙያዎች ላይ እርምጃ መውሰድ አንዱ የሙያዊ ሥነ-ምግባር አላማ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡